# የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የ1997 በጀት ዓመት የመንግሥት አጠቃላይ
# ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት
# (ረቂቅ ሪፖርት)

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1989 በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ የሂሣብ መረጃዎችን የበጀቱ ዓመት እንደተጠናቀቀ በተቻለ ፍጥነት ዘግቶ ለኦዲት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደሚልክና የዋናው ኦዲተር መ/ቤትም የሂሣብ መግለጫው በደረሰው በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ኦዲት አድርጎ ሪፖርቱን ከነአስተያየቱ ለሚኒስቴሩ መላክ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረበውን የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የኢትዮጵያ የመንግሥት ሂሳብ የኦዲት ደረጃዎችን (Ethiopian Government Audit Standards) ተከትለን ኦዲት አድርገናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የፌዴራል መንግሥት የ1998 በጀት ዓመት የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ፣ የሂሣብ መዛግብት ሰነዶችና ሌሎች የሂሣብ መግለጫዎች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሂሣብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን፣ ዝርዝር የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ህጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን በመከተል መፈፀማቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡

በአዋጅ ቁጥር 68/1989 መሠረት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተዘጋጁት የመንግሥት ሂሣብ መግለጫዎች የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው መዘጋጀታቸውን በኦዲት በማረጋገጥ ነፃ አስተያየት መስጠትና ሪፖርት ማቅረብ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ ሂሣቦች ላይ የተከናወነ ሲሆን የተሟላና ተገቢ ማስረጃ መኖሩን፣ የፋይናንስ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተከብረውና የውስጥ ቁጥጥር

ሥርዓቶች ተጠብቀው ዝርዝር የሂሣብ እንቅስቃሴዎች መፈፀማቸውን እና የሂሣብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ያካተተ ነው፡፡

የቀረበውን የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ እንዲያስችለን ጉልህ የሆኑ ስህተቶች አለመፈፀማቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ የተሟላ ማስረጃና ማብራሪያ ለማግኘት በሚያግዝ ደረጃ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

አስተያየታችንን ለመስጠት እንዲያስችለን በሂሣብ መግለጫው የቀረበው የበጀት ዓመቱ የገቢና የወጪ ሂሣብ፣ እንዲሁም የሂሣብ ማስረጃ ጥንቅርና አመዘጋገብ ሲታይ፣

1. ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተላለፈው የድጋፍና ልዩ ድጎማ በጀት ብር 5,845.7 ሚሊዮን የሂሳብ ሪፖርት ሳይቀርብ በቀጥታ ሥራ ላይ እንደዋለ ተደርጎ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

   የቀረበውም ዓመታዊ የገቢና ወጪ ሂሣብ ሪፖርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 መሠረት የክልል መንግሥታት እና የከተማ መስተዳድሮች የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ በሚያሳይ መልኩ አልተዘጋጀም፡፡

   ይህንን አስመልክቶ የመጨረሻ እልባት ለመስጠት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ውይይት ተደርጓል በዚህም መሠረት ከሂሳብ አያያዝ እና ከኦዲት አንፃር በማየት ሂሳቡ በወጪ የሚመዘገብበትን ሁኔታ የሚያጠና ከሚኒስቴር መ/ቤቱና ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተውጣጡ አባላት ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

2. በአዋጅ ቁጥር 25/84 እንደገና የተቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የመንግሥት ዋና ገንዘብ እና የዘቀጠ ትርፍ ክፍያ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/84 ያልተቋቋሙት ደግሞ የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 163/71 ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1987 አስቀድሞ ያልተከፈለ ውዝፍ የዋና ገንዘብ ክፍያ እና የዘቀጠ ትርፍ እንዲሁም ከማሻሻያ አዋጅ ጀምሮ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት የዘቀጠ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በነዚህ አዋጆች መሠረት ከእያንዳንዱ ድርጅት ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የ83 ድርጅቶች ሌጀር ለኦዲት የቀረበ ቢሆንም እነዚህ ድርጅቶች ያለባቸውን የካፒታል ቻርጅና የዘቀጠ ትርፍ ውዝፍ ዕዳ ያልከፈሉ ከመሆኑም በላይ የመክፈል አቅም የሌላቸው በመሆኑ የዕዳ ስረዛ እንዲደረግላቸው 15 ድርጅቶች ተለይተው የተያዙ ቢሆንም፣ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለውሳኔ ቀርቦ በህግ ክፍል የተያዘ መሆኑና ሂሳቡ እንዲሰረዝ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል::

እዳቸውን መክፈል ይችላሉ ተብለው ከተለዩት ድርጅቶች መካከል ደግሞ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሌሉ ድርጅቶች ለምሳሌ እንደ ኤርትራ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ አስመራ ሹራብ ፋብሪካ፣ አስመራ ከረሜላ ፋብሪካ እና አስመራ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመሳሰሉት የሚገኙበት መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል:: በመሆኑም የእዳ ስረዛ ሊደረግላቸው የሚገባ ድርጅቶችና የመክፈል አቅም ያላቸው ድርጅቶች በአግባቡ ተለይተው ሂሳቡ የሚስተካከልበት ሁኔታ መፈለግ አለበት::

3. የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅትና አዲስ መካኒካል ኢንተርፕራይዝ ብድራቸውን በወቅቱ የከፈሉ ስለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከአዲስ መካኒካል ኢንተርፕራይዝ ያልተሰበሰበ ዋና ገንዘብ ብር 10,718,437.00 እና ብር 3,364,243.00 ከሁለቱ ድርጅቶች የሚፈለግ የወለድ ሂሳብ ተገኝቷል::

4. አዲስ መካኒካል ኢንተርፕራይዝ በብድር ስምምነቱ መሠረት የተፈቀደለት የብድር መጠን SDR 1,434,077 ሆኖ ሳለ SDR 1,476,182 ተሰጥቶ በመገኘቱ SDR 42,105 በብድር ስምምነቱ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ተከፍሎት ተገኝቷል::

5. በብድር አስተዳደር መምሪያ ተመዝግቦ የተያዘው መንግሥት ከውጭ አገር የተበደረው ሂሣብ በፌደራል መንግሥት አመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ በትክክል የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ግብርናና ገጠር ልማት ሚነስቴር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ በብድር ያገኘውን ብር 13.6 ሚሊዮን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ሂሳቡ በገቢ ያለመመዝገቡና በሂሳብ መግለጫው ውስጥ ያለመካተቱ ታውቋል::

6. በመልሶ ማበደር አማካኝነት ከመንግሥት ብድር ካገኙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ተሰብሳቢ የዋና ገንዘብና የብድር ወለድ ሂሳብ በቀረበው የመንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ውስጥ አልተካተተም::

7. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ መሠረት የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይታወጅ የተለያዩ ባለበጀት መ/ቤቶች በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች ብር 947.00 ሚሊዮን ከተደለደለው በጀት በላይ እንዲሁም በጀታቸውን ያልተጠቀሙበት ብር 4,060.73 ሚሊዮን ተገኝቷል። ከበጀት በላይ የተጠቀሙት መ/ቤቶች የተጠቀሙበትን ምክንያት የሚገልጽ ዘገባ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሂሳቡን በወጪ ከመመዝገብ በስተቀር ከበጀት በላይ በተጠቀሙ መ/ቤቶች ላይ ምንም የተወሰደ እርምጃ የለም። ይሁን እንጂ ለወደፊቱ ሁኔታውን ለማስተካከል የበጀት ዝውውር መመሪያ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተጠቅሷል።

8. በገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 25 (3) መሠረት በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ መንግሥት ከቀጥታ ብድር መበደር የሚችለው ባለፉት ሦስት ተከታታይ በጀት ዓመታት ውስጥ ከተሰበሰበው አማካይ የመንግሥት መደበኛ ገቢ ከ15% መብለጥ እንደሌለበት የተደነገገ ሲሆን፣ በ1994፣ በ1995 እና በ1996 በጀት ዓመታት የተሰበሰበ አማካኝ መደበኛ ገቢ ብር 9,336.8 ሚሊዮን ነው። የዚህ 15% ደግሞ ብር 1,400.5 ሚሊዮን ሲሆን፣ በ1997 በጀት ዓመት መንግሥት ከቀጥታ ብድር የተበደረው ብር 9,212.0 ሚሊዮን መሆኑ ተረጋግጧል። በመሆኑም በአዋጅ ከተፈቀደው በላይ ብር 7,811.5 ሚሊዮን የቀጥታ ብድር የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል። በሌላም በኩል በ1997 በጀት ዓመት ከቀጥታ ብድር ብቻ የተገኘው ብድር በ1997 በጀት ዓመት የበጀት ዓዋጅ ላይ ከተመለከተው ጠቅላላ የአገር ውስጥ ብድር በጀት ብር 1,694.4 ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ብልጫ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአገር ውስጥ ብድር የገንዘብና የባንክ አዋጅንም ሆነ የበጀት ዓዋጁን ሳይከተል የተፈጸመ መሆኑን ነው።

9. የውጭ አገር ብድር ዕዳ ክፍያ በውል ስምምነቱ መሠረት መፈጸሙንና ሂሳቡም በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ /አርዕስት/ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት በተደረገበት ወቅት ብር 17.46 ሚሊዮን ከውጭ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች የቅድሚያ ፍተሻ አገልግሎት ኤስጂኤስ (SGS) ለተባለ ድርጅት ለውጭ አገር ብድር የዋና ዕዳ ክፍያ ከተያዘው በጀት ላይ ተከፍሎ ተገኝቷል።

10. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቻናል 2 የተገኘን እርዳታ በሂሳብ መግለጫው ውስጥ ለማካተት እያንዳንዱ መ/ቤት ያገኘውን እርዳታ እንዲያሳውቅ ደብዳቤ መፃፍ፣ የተለየ የእርዳታ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማድረግ እና መ/ቤቶች በእርዳታ ያገኙትን ገንዘብ ሥራ ላይ አውለው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ

በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ሪፖርት ሲያቀርቡ ሂሳቡን የመመዝገብ ተግባር እያከናወነ ቢሆንም፣ ባለበጀት መ/ቤቶች በቻናል 2 ያገኙትን እርዳታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁ ቢቀሩ ሪፖርት ያላደረጉትን መ/ቤቶች ለማወቅና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ባለመኖሩ በቀረበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የእርዳታ ገቢ ሂሳብ መንግሥት በበጀት ዓመቱ ያገኘው ዕርዳታ ይህ ብቻ ነው ብሎ ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡ ለወደፊቱ አሰራሩን ለማሻሻል ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መመሪያ መተላለፉን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

11. የበጀት ዓመቱ የተስተካከለ በጀት በዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ ላይ በትክክል መያዙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ብር 61.14 ሚሊዮን በዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ ውስጥ በተጨማሪ በጀትነት ሳይካተት ቀርቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 11 በዝርዝር ከተገለፁት ልዩ ልዩ የአሰራር ግድፈቶች በስተቀር በእኛ አስተያየት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የቀረበው የመንግሥት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የዘመኑን የመንግሥት ሂሣብና የፋይናንስ አፈፃፀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ግኝቶች ዝርዝር ሁኔታዎችና የመፍትሄ ሀሳቦች በሪፖርቱ ከገጽ 6 ጀምሮ ተመልክቷል፡፡

# የ1997 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት
# አጠቃላይ ዓመታዊ የገቢና የወጪ
# ሂሣብ ኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቀረበው አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የበጀት ዓመቱ የገቢና የወጪ ሂሳብ በበጀት አዋጅ መሠረት መሰብሰቡንና ወጪ መሆኑን ሂሳቡም በትክክል የተመዘገበ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

## 1. የገቢ ሂሳብ

### 1.1 በበጀት ስለተያዘውና ስለተሰበሰበው ገቢ

በበጀት ዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ በበጀት ከተያዘው ገቢ ውስጥ ብር 6532 ሚሊዮን ሳይሰበሰብ መገኘቱ፣

በፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ የገቢ እቅድ በ1997 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ በነጋሪት ጋዜጣ የታወጀውና በተጨማሪ በጀት በተያዘው ብር 25528 ሚሊዮን ሲሆን የተሰበሰበው ብር 18966 ሚሊዮን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ብር 6532 ሚሊዮን ያልተሰበሰበ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በሚሊዮን

| የገቢው ዓይነት | የተስተካከለ በጀት | የተሰበሰበ ገቢ | የተሰበሰበ ገቢ በመብለጥ በማነስ |
|---|---|---|---|
| የታክስ ገቢ | **10,488** | **9,360** | **(1,128)** |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | **2,757** | **2,236** | **(519)** |
| የካፒታል ገቢ | **427** | **135** | **(292)** |
| የውጭ አገር እርዳታ | **6,442** | **5,339** | **(1,103)** |
| የውጭ አገር ብድር | **5,414** | **1,924** | **(3,490)** |
| ድምር | **25,528** | **18,996** | **(6,532)** |

ከላይ እንደተመለከተው ላልተሰበሰበው ብር 6,532 ሚሊዮን የሚመለከታቸው ክፍሎች በበጀት ዝግጅት ወቅት አስፈላጊው መረጃ ተጠናቅሮና ከፍተኛ ጥናት ተደርጎ የተዘጋጀ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ገቢው ሙሉ በሙሉ ሊሰበሰብ እንዳልቻለ ገልፀዋል፡፡

ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች በሰጡት መልስ በበጀት ዝግጅት ወቅት አስፈላጊ መረጃ ተጠናቅሮ ከፍተኛ ጥናት ተደርጎ የተዘጋጀ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ገቢው ሙሉ በሙሉ ሊሰበሰብ እንዳልቻለ ገልጸዋል፡፡

## 1.2 የኢንቨስትመንት ገቢ

መንግሥት ከልማት ድርጅቶች ሊሰበሰብ የሚገባው ከአዋጅ ቁጥር 25/1984 በፊት የነበረ ውዝፍ የዋና ገንዘብና የዘቀጠ ትርፍ እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 163/71 የሚተዳደሩ ድርጅቶች የሚፈለግባቸውን የዘቀጠ ትርፍና ከአዋጅ ቁጥር 121/87 በፊት የሚፈለግባቸውን የዋና ገንዘብ እየከፈሉ ለመሆኑና በአግባቡም የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

- የ83 ድርጅቶች ሌጀር የተከፈተና በየስማቸው ያለባቸው ውዝፍ እዳ ካፒታል ቻርጅና የዘቀጠ ትርፍ ከኦዲት ሪፖርት በመነሳት የተመዘገበ መሆኑ ታይቷል፡፡ ሆኖም ግን ውዝፍ እዳ ያለባቸው ድርጅቶች እነዚህ ብቻ ለመሆናቸው ለማረጋገጥ እንደማይቻል ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተገልጿል፡፡ በሌጀር ከተያዙት 83 ድርጅቶች ውስጥ 15 ድርጅቶች የመክፈል አቅም እንደሌላቸው ተገልፆ እዳቸው ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለውሳኔ ቀርቦ በህግ ክፍል የተያዘ መሆኑንና ሂሳቡ እንዲሰረዝ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የእዳ መከታተያ ሌጀር ተከፍቶላቸው እዳቸው ተመዝግቦ ከተገኙ ድርጅቶች ውስጥ የፈረሱ ለምሳሌ ኤርትራ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ አስመራ ሹራብ ፋብሪካ፣ አስመራ ከረሜላ ፋብሪካ፣ አስመራ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል ከነዚህ ድርጅቶች ሂሳብ ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ ስለማይታመን ለውሳኔ ቀርቦ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለምን እንዳልተደረገ ተጠይቆ ይህንን ማድረግ የሚችለው

የኘራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልሆነ ተገልጿል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መክፍል የሚችሉ ድርጅቶች እንዲከፍሉ ምን ክትትል እየተደረገ እንደሆነ ተጠይቆ በተሰጠው መልስ ከድርጅቶቹ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ስለሌለን በቀጥታ መገናኘት የሚችለው ኤጀንሲው ስለሆነ ክትትል የሚደረገውም በዚያው በኩል እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልሆነ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ግን ሂሳቡ እልባት ሊያገኝ ስለሚገባው መሰረዝ የሚገባው እንዲሰረዝ፣ ሊሰበሰብ የሚችለውም እንዲሰበሰብ የተቀናጀና የጋራ ጥረት የሚያስፈልገው ስለሆነ ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

## 1.3 የመልሶ ማበደር ሂሳብ

መንግሥት ከውጭ አገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነቶች ለልማት ድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ዋና ገንዘብ ብር 102,005,726.20 እንደዚሁም የወለድ ክፍያ ብር 70,957,408.74 ገቢ የተደረገ ለመሆኑ በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ ተመልክቷል፡፡

ይሁን እንጂ በመልሶ ማበደር አማካኝነት ከመንግሥት ብድር ካገኙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ተሰብሳቢ የዋና ገንዘብና የብድር ወለድ ሂሳብ በቀረበው የመንግሥት አጠቃላይ የሂሳብ መግለጫ ውስጥ አልተካተተም፡፡

## 1.4 በወቅቱ ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ ብር 14.08 ሚሊዮን

እስከ ሰኔ 30/1997 ዓ.ም ድረስ አዲስ መካኒካል ኢንተርኘራይዝ ያልተሰበሰበ የዋና ገንዘብ ብር 10.7 ሚሊዮን፣ እንዲሁም ከምርጥ ዘር ድርጅትና ከአዲስ መካኒካል ኢንተርኘራይዝ የብድር ወለድ ብር 3.4 ሚሊዮን በድምሩ ብር 14.08 ሚሊዮን ተገኝቷል፡፡ በወቅቱ ያልተሰበሰበውም ሂሳብ በዓመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫው ውስጥ አልተካተተም፡፡

በብድር ስምምነቱ መሠረት ተመላሽ ያልተደረገውን ሂሳብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ አበዳሪዎች ወቅቱን ጠብቆ ክፍያ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ሲሆን

ዕዳው የተከፈለላቸው ድርጅቶች ደግሞ በገቡት ውል መሠረት ያለባቸውን የመንግሥት ዕዳ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ግዴታቸውን በማይወጡ ድርጅቶች ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ በመውሰድና ክትትል በማድረግ የመንግሥት ገንዘብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲሰበሰብ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

### 1.5 <u>በብድር ስምምነት ላይ ከተጠቀሰው በላይ ተከፍሎ የተገኘ</u>

ለአዲስ መካኒካል ኢንተርኘራይዝ በስምምነቱ መሠረት የተፈቀደለት SDR 1,434,077 ሆኖ ሳለ SDR 1476182 ተሰጥቶ በመገኘቱ SDR 42,105 በብልጫ የተሰጠው መሆኑ ታውቋል፡፡ ኦዲት አስደራጊዎች በሰጡት ምላሽ ችግሩ የተከተሰው በአበዳሪዎችና በተበዳሪው መካከል በተደረገው ስምምነት ሊሆን እንደሚችል የተገለጸ ቢሆንም የብድር ስምምነት የሚፈረመው በአበዳሪውና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መካከል በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በተጨማሪ ለተሰጠው የብድር መጠን አዲስ የብድር ስምምነት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

## 2. <u>የአገር ውስጥ ብድር ሂሳብ</u>

መንግሥት የሚያጋጥመውን የበጀት እጥረት ለመሸፈን አገር ውስጥ ከሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት የተበደረው ሂሳብ በገንዘብና የፋይናንስ አዋጅና በበጀት አዋጅ መሠረት መፈጸሙን እንዲሁም ሂሳቡ በትክክል በገቢና በወጪ መመዝገቡና በዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ መካተቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ሁኔታ ተገኝቷል፡፡

### 2.1 <u>ከመበደሪያ ጣሪያ በላይ የተፈጸመ የአገር ውስጥ ብድር</u>

በገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 25/3/ መሠረት በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ መንግሥት ከቀጥታ ብድር መበደር የሚችለው ባለፉት ሶስት ተከታታይ በጀት ዓመታት ውስጥ ከተሰበሰበው አማካይ የመንግሥት መደበኛ ከ15% መብለጥ እንደሌለበት የተደነገገ ሲሆን፣ በ1994፣ በ1995 እና በ1996 በጀት ዓመታት የተሰበሰበ አማካኝ መደበኛ ገቢ ብር 9,336.8 ሚሊዮን ነው፡፡ የዚህ 15% ደግሞ ብር 1,400.5 ሚሊዮን ሲሆን በ1997 በጀት ዓመት መንግሥት ከቀጥታ ብድር የተበደረው ብር 9,212.0 ሚሊዮን መሆኑ

ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ከተፈቀደው በላይ ብር 7,811.5 ሚሊዮን የቀጥታ ብድር የተፈፀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

በሌላም በኩል በ1997 በጀት ዓመት ከቀጥታ ብድር ብቻ የተገኘው ብድር በ1997 በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ላይ ከተመለከተው ጠቅላላ የአገር ውስጥ ብድር በጀት ብር 1,694.4 ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ብልጫ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የቀጥታ ብድር የገንዘብና የባንክ አዋጁን ሳይከተል የተፈጸመ መሆኑን ነው፡፡ ስለሁኔታው የብድር አስተዳደር መምሪያ ተጠይቆ ጉዳዩን የሚከታተለው ብሔራዊ ባንክ ስለሆነ በመምሪያው በኩል የሚደረግ ክትትል ያለመኖሩን ገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የብድር አፈፃፀሙ በወጣው አዋጅ መሠረት መከናወን ያለበት ስለሆነ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

## 3. የውጭ አገር ብድር

በብድር አስተዳደር መምሪያ በኩል ተመዝግቦ የተያዘው መንግሥት ከውጭ አገር የተበደረው ሂሣብ በፌዴራል መንግሥት ዓመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ በትክክል የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ብር 13,650,470 ተጠቃሚው መ/ቤት ገንዘቡን ስለመቀበሉ ሪፖርት ያላደረገና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርም በሚዘጋጀው ማጠቃለያ ሪፖርት ላይ የብድሩ ሂሳብ በገቢ ያልተያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ተገኘ ተብሎ የተያዘው የብድር መጠን በዚሁ ልክ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለምን ሪፖርት እንዳልተደረገ ተጠይቆ ገቢው በ1997 በጀት ዓመት የተገኘ ቢሆንም በዚሁ በጀት ዓመት ሪፖርት እንዳልተደረገና በ1998 በጀት ዓመት ሪፖርት እንደተደረገ መ/ቤቱ ገልጿል፡፡ ሆኖም ግን የበጀት ዓመቱ የብድር ገቢ ከአበዳሪው ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት የብድሩ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ያገኙትን ብድር ብድሩ በተገኘበት በጀት ዓመት ሪፖርት እንዲያደርጉ ክትትል መደረግ ያለበትና በማጠቃለያ ሪፖርትም ሳይያዝ እንዳይታለፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 4. የውጭ አገር ዕርዳታ ሂሳብ

### 4.1 የውጭ አገር ዕርዳታ ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ለክትትል የማያመች ስለመሆኑ

በበጀት ዓመቱ መንግሥት በዕርዳታ ያገኘው ገቢ በሙሉ በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተካተተ መሆኑን ለማጣራት ተሞክሮ በቻናል 2 (Channel 2) ዕርዳታ ያገኙ ድርጅቶች ካቀረቡት ወርኃዊ ሪፖርት በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገባውን የዕርዳታ መጠን የሚገልፅ ማስረጃ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ሊቀርብ አልቻለም፡፡

በበጀት ዓመቱ ያገኙትን የዕርዳታ መጠን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በወርኃዊ ሪፖርት አማካኝነት ያላሳወቁ መ/ቤቶች ቢኖሩ የነዚህ መ/ቤቶች ሂሳብ መግለጫው ውስጥ ሳይካተት የሚቀር በመሆኑ የበጀት ዓመቱ የዕርዳታ ገቢ በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው ብቻ ይሆናል ለማለት አዳጋች ነው፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ሂሳብ ለመከታተል ባለበጀት መ/ቤቶች ያገኙትን ዕርዳታ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ የሚጠይቅ መሆኑን፣ የተለየ የባንክ ሂሳብ በባለበጀት መ/ቤቶች እንዲከፈት ማድረጉን እና ያገኙትን እርዳታ ሥራ ላይ አውለው ሪፖርት ሲያቀርቡ በተጨማሪ በጀትነት እየተመዘገበ እንደሆነ ቢታወቅም፤ ዕርዳታ አግኝተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ያላደረጉ መ/ቤቶች ቢኖሩ ሊታወቅ የሚችልበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመልቲላተራል እና የመንግሥታት ትብብር መምሪያዎች ከዕርዳታ ሰጪዎች ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ወደ አገር ውስጥ የገባውን የገንዘብ እና የዓይነት እርዳታ መጠን ለማወቅ የሚያስችል መረጃ የሚይዙ ሲሆን፣ የማዕከላዊ ሂሳብ መምሪያ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ዕርዳታ ደርሷቸው ሪፖርት ያላቀረቡ መ/ቤቶችን በመከታተል ትክክለኛውን የዕርዳታ ብድር መጠን መመዝገብና በዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ ላይ ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 5. የወጪ ሂሳብ

በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የወጪ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማጣራት በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 5.1 በቀጥታ ወጪ ተይዞ ስለተገኘው ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተሰጠ ሂሳብ ብር 5,845.7 ሚሊዮን

በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የድጎማ ወጪ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ የሚገልጽ የሂሳብ ማስታወቂያ የቀረበለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ ለክልሎችና ለከተማ መስተዳድሮች የተከፈለ ብር 5,845.7 ሚሊዮን ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ሳይረጋገጥና ሪፖርት ሳይቀርብለት በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 እና አንቀጽ 74 (4) የመንግሥት ሂሳብ ሪፖርት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የተደረጉትን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች፣ የክልል መንግሥታትን የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ የበጀት ዓመቱን የመጨረሻ ሪፖርት በተጠቃለለና በተነፃፀረ መልኩ የሚይዝ እንደሚሆን እና የክልል መንግሥታትም ከፌዴራል መንግሥት የተሰጣቸውን የበጀት ድጋፍና የውስጥ ገቢያቸውን በየወሩና በየሩብ ዓመቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ እንዳለባቸው በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የድጎማ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ሳይታወቅ የተዘጋጀው የመንግሥት ዓመታዊ የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫ አቀራረብ ለፖሊሲ አውጪው አካል አሳሳችና የአገሪቱን ትክክለኛ ዓመታዊ ገቢና ወጪ አጠቃሎ የማያሳይ በመሆኑ መታረም እንዳለበት ባለፉት ዓመታት የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ለመስጠት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ውይይት በማድረግ ሂሳቡ በወጪ የሚመዘገብበትን ሁኔታ የሚያጠና ከፌዴራል ዋናው ኦዲተርና ከሚኒስቴር

መ/ቤቱ የተውጣጡ አባላት ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በመስራት ላይ ይገኛል።

## 5.2 በልዩነት ስለተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

ባለበጀት መ/ቤቶች የሚያቀርቡት ወርሃዊ ሪፖርት በትክክል ተመዝግቦ በመንግሥት አጠቃላይ የሂሳብ መግለጫ ውስጥ መካተቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባቀረበው ወርኃዊ የሂሳብ ሪፖርት ሃያ የሂሳብ አርዕስቶች በብልጫና በማነስ ተመዝግቦ ተገኝቷል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።

| ተራ ቁ. | የመ/ቤቱ ኮድ | የወጪ አርዕስት | በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተመዝግቦ የተገኘ | መ/ቤቱ ባቀረበው ወርኃዊ ሪፖርት መሠረት | ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት የመዘገበው በመብለጥ(በማነስ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 151/01/02 | 6211 | 299,828.73 | 323,323.44 | (23,494.71) |
| 2 | " | 6212 | 1,006,540.18 | 1,056,750.38 | (50,210.20) |
| 3 | " | 6213 | 739,712.62 | 776,400.53 | (36,687.91) |
| 4 | " | 6217 | 2,180,479.23 | 2,264,453.69 | (83,974.46) |
| 5 | " | 6218 | 569,833.26 | 603,662.41 | (33,829.15) |
| 6 | " | 6219 | 193,616.54 | 170,616.37 | 23,000.17 |
| 7 | " | 6231 | 1,630,530.72 | 1,173,668.10 | 83,137.38 |
| 8 | " | 6233 | 3,145,301.31 | 3,273,231.31 | (127,930.00) |
| 9 | " | 6241 | 1,885,880.53 | 1,949,463.16 | (63,582.63) |
| 10 | " | 6243 | 648,726.92 | 676,319.45 | (27,592.53) |
| 11 | " | 6244 | 2,824,766.94 | 2,948,381.78 | (123,614.84) |
| 12 | " | 6251 | 13,171,278.94 | 19,421,278.74 | (4,250,000.00) |
| 13 | " | 6255 | 893,951.45 | 936,078.66 | (42,327.21) |
| 14 | " | 6256 | 10,157,119.67 | 9,156,583.96 | (1,000,535.71) |
| 15 | " | 6257 | 3,637,709.21 | 4,603,674.36 | (965,965.15) |
| 16 | " | 6258 | 6,143,304.80 | 6,033,785.35 | 109,519.45 |
| 17 | " | 6259 | 1,755,613.18 | 1,550,400.67 | 205,212.51 |
| 18 | " | 6313 | 341,561.07 | 239,505.91 | 102,055.16 |
| 19 | " | 6414 | 135,191.49 | 88,928.38 | 46,263.11 |
| 20 | " | 6419 | 4,523,441.38 | -- | 4,523,441.38 |
| | | | 55,884,187.97 | 55,786,506.65 | 9,7981.32 |

ስለሁኔታውም የሚመለከታቸው ተጠይቀው በምዝገባ ስህተት የተከተሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም የሂሳብ መግለጫው በዚሁ መሠረት መስተካከል ይኖርበታል፡፡

## 6. የበጀት አፈጻጸም በተመለከተ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባቀረበው የ1999 በጀት ዓመት የፌዴራል የመንግሥት ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መሠረት የተስተካከለ በጀት ብር 27,233.55 ሚሊዮን ነው፡፡ በሥራ ላይ የዋለው ብር 22,967.10 ሚሊዮን ወይም የበጀቱ 84.33% ይሆናል፡፡

ሥራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ወጪ የተደረገው ብር 8619.54 ሚሊዮን ከተስተካከለው መደበኛ በጀት ብር 9,654.13 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 1034.59 ሚሊዮን ወይም 10.72% በማነስ ታይቷል፡፡

ለካፒታል በጀት ወጪ የተደረገው ብር 8,501.82 ሚሊዮን ከተስተካከለው በጀት ብር 11,129.67 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 2,627.85 ሚሊዮን ወይም 23.61% ያነሰ ነው፡፡

ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተሰጠው ጠቅላላ ድጋፍ ብር 5,845.75 ሚሊዮን ከተስተካከለው በጀት ብር 6,439.90 ሚሊዮን ብር ጋር ሲነፃፀር በብር 594.15 ሚሊዮን ወይም 9.22% አንሶ ተገኝቷል፡፡ የበጀት ዘመኑ ጠቅላላ ወጪ ብር 22,967.10 ሚሊዮን ከ1996 በጀት ብር 19,978.20 ጋር ሲነፃፀር ደግሞ ብር 2,988.91 ወይም 13.01% ብልጫ አለው፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| የበጀት ዓይነት | የ1997 በጀት ዓመት | | | ልዩነት ከተስተካከለው በጀት በመብለጥ/ በማነስ | የ1996 በጀት ወጪ | የ1996 ከ1997 ወጪ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የታወጀ በጀት | የተስተካከለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ ወጪ | | | |
| መደበኛ | 8,140.00 | 9,654.13 | 8,619.54 | 1,034.59 | 8,410.20 | 209.34 |
| ካፒታል | 7,565.84 | 11,129.67 | 8,501.82 | 2,627.85 | 6,255.10 | 2,246.72 |
| የክልሎች ድጋፍ | 6,364.20 | 6,439.90 | 5,845.75 | 594.15 | 5,312.90 | 532.85 |
| | 22,070.04 | 27,223.70 | 22,967.11 | 4,256.59 | 19,978.20 | 2,988.91 |

ከላይ በሰንጠረዥ የተመለከተው በፌዴራል መንግሥት ዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ ላይ የተመለከተ የበጀት አፈጻጸም በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 እና ደንብ ቁጥር 17/89 መሠረት መከናወኑ ን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመለከተው ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

## 6.1 <u>ለእያንዳንዱ የወጪ ሂሣብ መደብ ከተደለደለው በጀት በላይ ስራ ላይ ስለዋለው ብር 953.8 ሚሊዮን</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀጽ 18/1 መሠረት በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር መደበኛ በጀትን በሚመለከት በዋና ሂሳብ መደቦች ውስጥ የሚደረግ ዝውውር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እየቀረበ ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ በአብዛኞቹ ባለበጀት መ/ቤቶች በአዋጁ መሠረት የጀት ዝውውር ጥያቄ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር አቅርበው ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ብር 947. ሚሊዮን እንዲሁም የተደለደለ በጀት ሳይኖር ሥራ ላይ የዋለ ብር 6.80 ሚሊዮን በድምሩ ብር 953.8 ሚሊዮን ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ 1 ተመልክቷል/፡፡

ስለጉዳዩ ባለበጀት መ/ቤቶች ባቀረቡት ዘገባ መሠረት የተለያዩ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ያለፉት ዓመታት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቀጣዩ በጀት ዓመት በወጪ በመመዝገቡ፣ የበጀት መዝጊያ ጊዜ በመሆኑና ክፍያዎች የግዴታ መስተናገድ ስለነበረባቸው እንዲሁም ሌሎች ምክንያቶች መ/ቤቶች ካቀረቡት ዘገባ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ የተደለደለው በጀት በቂ በማይሆንበትም ጊዜ ሆነ፣ በበጀት አዋጅ ወይም የበጀት ድልድል ውስጥ ያልተካተቱ ወጪዎች ሲያጋጥሙ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 እና ደንብ ቁጥር 17/89 መሠረት እርምጃ መውሰድ ሲገባ ባለበጀት መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጪ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ መጠቀማቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም ከተፈቀደላቸውም ሆነ ከተደለደለው በጀት በላይ በሚጠቀሙ መ/ቤቶች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበት አሠራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

## 6.2 ለእያንዳንዱ ዋና ዋና የሂሣብ መደብ ተደልድሎ ሥራ ላይ ሳይውል የተገኘ ብር 4060.73 ሚሊዮን

የታወጀው በጀት የመ/ቤቶችን ዓመታዊ እቅድ ታሳቢ በማድረግ በተደለደለው በጀት መሠረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለልዩ ልዩ ዋና ዋና የሂሳብ መደቦች ከተደለደለላቸው በጀት ውስጥ ከብር 6 ሚሊዮን በላይ የተደለደለላቸውን በጀት ሥራ ላይ ሳያውሉ ከተገኙ 91 መ/ቤቶች ብቻ ብር 4,060.73 ሚሊዮን ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ 2 ይመልከቱ/፡፡

ከዚህ ውስጥ ብር 2,416.16 ሚሊዮን የተስተካከለ በጀት ኖሯቸው ፈጽሞ በጀታቸውን ያልተጠቀሙ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የሚያቀርቡት የበጀት ጥያቄ በተጨባጭ ሊሰራ ከታቀደው ዓመታዊ የሥራ እቅድ ጋር በማገናዘብ እና ያለፉትን ዓመታት አፈጻጸም በመገምገም የማይሰሩበትን በጀት ያለአግባብ በሚጠይቁ መ/ቤቶች ላይ ተገቢውን ክትትል ከማድረግ የበጀት ዝግጅትና አፈቃቀድ ሥርዓቱን ማሻሻል ተገቢ ነው፡፡

## 6.3 በጀት ሳይያዝለት ለአገልግሎት የተከፈለ ሂሳብ ብር 17.46 ሚሊዮን

የውጭ አገር ብድር የዋና ገንዘብና ወለድ ክፍያ በብድር ስምምነቱ መሠረት መፈፀሙንና ሂሣቡም በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ /አርዕስት/ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት በተደረገበት ወቅት ብር 17.46 ሚሊዮን ከውጭ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች የቅድሚያ ፍተሻ አገልግሎት ለኤስጂኤስ (SGS) ለተባለ ለውጭ ድርጅት አገር ብድር የዋና ዕዳ ክፍያ ከተያዘው በጀት ላይ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ስለሁኔታውም ከብድር አስተዳደር መምሪያ በተሰጠው መልስ ክፍያው ሊፈጸም የቻለው አይዲኤ (IDA) ከውጭ አገር ላስገባቸው እቃዎች ለተሰጠ አገልግሎት ሲሆን ድርጅቱ ስራውን እንዲያቋርጥ በተደረገበት ወቅት ለድርጅቱ ሳይከፈል የቀረውን ገንዘብ ከብዙ ድርድር በኋላ ለድርጅቱ ያልተከፈለ ዕዳ የአሜሪካ ዶላር 2 ሚሊዮን መሆኑን ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ ዕዳ በ1997 በጀት ዓመት ከብድር አስተዳደር መምሪያ ከውጭ አገር የዕዳ ክፍያ በጀት ላይ እንዲከፈል መደረጉን ነገር ግን በኛ

በኩል ከውጭ ሀገር የዋና ገንዘብ ክፍያ ያልተያዘ ሂሳብ ነው ብለው የገለጹ ሲሆን ከማዕከላዊ ሂሳብ መምሪያ በተሰጠው መልስ ደግሞ ከትሬዠሪ መምሪያ ለብሔራዊ ባንክ በሚጻፈው የክፍያ ትዕዛዝ ደብዳቤ መሠረት ክፍያውን በዚሁ የወጪ ሂሳብ አርዕስት ሊመዘገብ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

የተፈጸመው ክፍያ በአግባቡ በጀት ሊያዝለት ሲገባ ከውጭ አገር የዋና ገንዘብ ዕዳ ክፍያ በጀት ላይ የተፈጸመ በመሆኑ ለሂሳቡ አስፈላጊውን የሂሳብ ማስተካከያ እንዲደረግለት እናሳስባለን፡፡

## 6.4 <u>በዓመታዊ የገቢና ወጪ ሪፖርት ማጠቃለያ ውስጥ ያልተያዘ የተጨማሪ በጀት ሂሳብ ብር 61.14 ሚሊዮን</u>

የበጀት ዓመቱ  የተስተካከለ በጀት በትክክል በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሪፖርት ላይ መያዙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ብር 61.14 ሚሊዮን በሪፖርቱ ማጠቃለያ ውስጥ በተጨማሪ በጀትነት ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ ስለሁኔታውም የሚመለከታቸው ሠራተኛ ተጠይቀው ሂሳቡ በተጨማሪ በጀትነት ያልተያዘ መሆኑን በአመዘጋገብ ስህተት ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም የሂሳብ መግለጫው ያልተያዘውን ተጨማሪ በጀት በማካተት መስተካከል ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡